የሰ/መ/ቁ. 119500

ሐምሌ 22 ቀን 2008 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሽምሱ ሲርጋጋ

አብረሃ መሰለ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ፀሀይ ውብዬ } አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** የፌደራል/ዓ/ህግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመንግስት ማህተምን ያለአግባብ መገልገል ሙከራ ወንጀል የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች እና አብረዋቸው በተከሰሱ ተከሳሾች ላይ ባቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ላይ የቀረበው ክስ ይዘት ተከሳሽ ለመንግስት ስራ የሚውል ማህተምን ያላግባብ ለመገልገል አስባ በዐ/ህግ 3ኛ ምስክር አማካኝነት ለወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል (1ኛ ተከሳሽ) 1000 ብር ከፍላ የኢት/ንግድ ባንክን ማህተም ከባንኩ ሰርቃ እንድታመጣላት ካደረገች በኃላ በምስክሯ ጥቆማ የተያዘች በመሆኑ የወ/ህ/አ 27(1) እና 363 (1)(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ የመንግስት ማህተም ያለአግባብ መገልገል ሙከራ ወንጀል ተከሰላች የሚል ነው፡፡

አመልካች (የስር ተከሳሽ) በክሱ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመካዳቸው ዐ/ህግ ማህተሙ የጠፋበት የኢት/ን/ባንክ ሱማሌ ተራ ቅርንጫፍ ሠራተኞችን ጨምሮ 3 ምስክሮችን አሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱ ከዐ/ህግ ምስክሮች 1ኛ ተከሳሽ የሆኑት ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በተጨማሪ ምስክርነት ሰምቶ አመልካች ክሱ የቀረበበትን የወንጀል ድርጊት ለመፈፀማቸው የተመሰከረባቸው በመሆኑ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ሲሆን አመልካች የሰው

መከላከያ ማስረጃ የለኝም በሚሮን ሚካኤል የግል ስልክ በወቅቱ ስለመደወሌ ከኢት/ቴሌኮም ዝርዝር ቀርቦ ይታይልኝ ብለዋል፡፡

ፍ/ቤቱ ከሰኔ ወር መጀመሪያ እስከ ሐምሌ ወር መጨረሻ 2006 ዓ/ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በግል ስልካቸው የተደወለ የስልክ ቁጥር ዝርዝር እንዲቀርብ ባዘዘው መሠረት ከኢት/ቴሌኮም በቀረበው ዝርዝር ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል በሚጠቀሙበት ስልክ ቁጥር አመልካች በሚሰሩበት የመከላከያ ሚ/ር የቢሮ ስልክ ቁጥር ላይ ተደውሎ የነበረ መሆን አለመሆኑን ባያሳይም ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤል ስልክ ላይ ተከሳሽ አልደወለችም ብሎ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያዳግት ነው በማለት አመልካች (ተከሰሽ) በተከሰሱበት የወንጀል ህግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ናቸው ብሎ በመወሰን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በማገናዘብ በቅጣት አወሰሰን መመሪያው ቅጣቱን በማስላት በ3 ዓመት ከ3 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለፌ/ክልል ፍ/ቤት በይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች ላይ በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔን በማፅናት ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ እና በመንግስትና በህዝብ ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመኖሩ ስር ፍ/ቤት የወንጀሉን ደረጃ በቀላል ደረጃ መመደብ ሲገባው መካከለኛ ደረጃ መመደቡ ተገቢ አይደለም ብሎ የወንጀሉን ደረጃ በቀላል ደረጃ በመመደብ መነሻ ቅጣት 3 ዓመት ወስኖ በ2 ማቅለያ ምክንያቶች ቅጣቱ ወደ 2 ዓመት ፅኑ እስራት በማሻሻል ወስኗል፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ ተፈፀመ ያሉትን መሠረታዊ የህግ ስህተት በመጥቀስ እንዲታረምላቸው የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች በስር ፍ/ቤቶች ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት የተወሰነባቸው በክሱ ላይ የተጠቀሰውን የህግ አንቀጽ የሚያቋቁም ድርጊት መፈፀማቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ መሆን አለመሆኑን እና በዚህ ጉዳይ በስር ፍ/ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩትና ወ/ሮ ሜሮን ሚካኤልን በአመልካች ክስ በማጣሪያ ምስክርነት ጠርቶ የመስማቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች ተከሰው ጥፋተኛ የተባሉት የወ/ህጉን አንቀጽ 27(1) እና 363 (1) "ለ" የተመለከተውን ተላልፈው ለመንግስት ስራ በተዘጋጀ ማህተም ያለ አግባብ መገልገል ሙከራ ወንጀል ሲሆን የድንጋጌው ይዘት ለመንግስት ስራ ጉዳይ ብቻ የሚታተምበትን የመንግስትን ወይም የመንግስታዊ አካላት የአንዱን ማህተም ያለአግባብ የተገለገለ እንደሆነ ከ3 ዓመት እስከ 10 ዓመት ሊደርስ

በሚችል ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ አመልካች ለኢት/ንግድ ባንክ ሱማሌ ተራ ቅርንጫፍ መገልገያነት የተዘጋጀውን የመንግስት ማህተም በተጠሪ 3ኛ ምስክር እና በስር 1ኛ ተከሳሽ በሆኑት የባንኩ ተላላኪ ሠራተኛ አማካኝነት ማህተሙን ተቀብለው የባንኩ ተላላኪ ሠራተኛ ለሆኑት የስር 1ኛ ተከሳሽ ብር 1000 መላካቸው ስር ፍ/ቤት በቀረበው ማስረጃ በማረገጋጥ አመልካች ላይ ያሳለፈው የጥፋተኛነት ውሳኔ በህጉ አግባብ በመሆኑ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም በሌላ በኩል አመልካች የተከሰሱት እና የጥፋተኛነት ውሳኔ የተላለፈባቸው በሙከራ ደረጃ በቀረ ወንጀል በመሆኑ በወ/ሕ/አንቀጽ 31 እንደተመለከተው ተከሳሹ ጥፋተኛ በተባለበት የሙከራ ወንጀል ድርጊት የደረሰ ጉዳት ከሌላ በወ/ህ/ቁ. 180 በተመለከተው መሠረት ቅጣቱን በመሰለው እንደሚያቀል የተደነገገ በመሆኑ እና በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ቀደም ሲል እንደነበረው የቅጣት አወሳሰን በሙከራ ደረጃ ለተፈጸመ ወንጀል ቅጣት እንደሚቀንስ በግልጽ ባይመለከትም በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 24 ስር በወንጀል ህጉ ቅጣትን በመሰለው እንዲያቀል በፈቀደ ጊዜ ፍ/ቤቱ በመመሪያው ሳይወሰን ቅጣትን በማቅለል እንደሚወሰን የተመለከተ በመሆኑ እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ በሰ/መ/ቁ. 104937 አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም የሰጠ በመሆኑ ወንጀሉ በሙከራ ደረጃ የቀረ መሆኑን መሠረት በማድረግ የስር ፍ/ቤት ቅጣቱን በመሰለው ማቅለል ሲገባው ይህን በማለፍ በቀረቡለት 2 ማቅለያ ምክንያቶች ላይ ብቻ በመወሰን የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ሊታረም የሚገባው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 121682 በቀን 6/11/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት እና የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 001102 በቀን 18/2/2008 ዓ/ም የሰጡት የጥፋተኛነት ውሳኔ እና ትዕዛዝ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 195(2) (ለ) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የፌ/ከፍ/ፍ/ቤት ያሳለፈው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
3. አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በሙከራ ደረጃ የቀረ እና በመንግስት ላይ የደረሰ ጉዳት ባለመኖሩ የወ/ህጉን አንቀጽ 27(1)፣31፣ 180፣ እና 363(1) (ለ) እንዲሁም የተሻሻለውን የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ. 2/2006 አንቀጽ 24 መሠረት በማድረግ ለአመልካች ስር ፍ/ቤት የተያዘላቸውን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችንም ከግምት በማስገባት አመልካች ለፈፀሙት ጥፋት ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የታሰሩበት የሚታሰብላቸው ሆኖ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ የስር ፍ/ቤትን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል ወስነናል፡፡

4. አመልካች ታስረው የሚገኙበት ማ/ቤት በዚህ በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሠረት እንዲያስፈጽም ይፃፍ ብለናል መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ